# የወያኔ መንግስት የትግራይን ሕዝብ የማስፈራሪያ ፕሮፓጋንዳውን ቢቀጥልም ትግሉ እስከ ወያኔ ውድመት ይቀጥላል!

ለወያኔው-ጠቅላይ ሚ/ር „የሕግ የበላይነት ሲመነዘር“ ምን ይመስላል? ይህንን ጽሁፍ ለማቅረብ ያነሳሳኝ እቶ ሃይለ ማርያም ቅንነት ባልተሞላበት መልክ ለተጠየቁት ዋና ዋና ጥያቄዎች አስመልክቶ ሲንሸራተት በማዳመጤና እስቲ እኔም የምለውን ልበል ለማለት ነው። በቅድሚያ ድንገት ኢሕአዴግ የሚለውን መጠሪያ ለመጠቀም ያልፈለኩት በወረቀት ላይ ያለና ምንም ይህ ነው የማይባል ህልውና የሌለው የወያኔ የገደል ማሚቱ በመሆኑና ዋናው አዛዥና ናዛዥ ወያኔ በመሆኑ ነው። የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስቴር ለማለትም የኢትዮጵያ ሕዝብ ነጻ በሆነ ምርጫ በፈቃዱ ያላስቀመጠው ባለስልጣንና ዴሞክራሲያዊ አሰራርን ተከትሎ ያልተመረጠ ራሱን በወያኔ ትዕዛዝ በሕዝብ ስም ያስቀመጠ ግለሰብ በመሆኑ ነው። ይህን ካልኩ በኋላ ለጋዜጠኞች የወያኔው ጠቅላይ ሚኒስቴር ከሰጣቸው መግለጫዎች ውስጥ የሕግ የበላይነት፣ ሙስናና ተጠያቂነትን አስመልክቶ ያላቸው ላይ ትኩረት መስጠት እሻለሁ።

1. የወያኔ ሕገ-መንግስትና የወያኔ ባለስልጣናት ወያኔ የወያኔን ሕገ-መንግስት እሱ በሚመስለው መልክ አቅርቦ፣ እሱ በሚስማማው መልክ አውጇል። ይህንን ሕገ-መንግስት የወያኔ ባለስልጣናት ለ 25 ዓመታት በመጣስና ሌሎች እርምጃዎችን በመውሰድ ይታወቃሉ። ለምሳሌ የተቃዋሚ ፖለቲካ ድርጅቶችን የመሰብሰብ መብት፣ አዳራሽ በመከልከል፣ ስብሰባውን በማገድ፣ ሰላማዊ የሆነ የተቃውሞ ስልፎችን በመከልከል፣ . . . ወዘተ የምርጫ ሂደቶችንና ውጤቶችን በግልጽ በማጭበርበር፣ የወያኔው ፍርድ ቤት የወሰነውን ውሳኔ ባለመቀበል፣ የወሰነውን ውሳኔ በመናቅ ግለሰቦችን እንደገና ማሰር፣ ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ ማሰር፣ ዜጎችን አስሮ በማሰቃየት፣ ወዘተ የወያኔ ባለስልጣናት ይታወቃሉ።

ጋዜጠኞችን የተለየ አስተሳሰብ በመጻፋቸው ወይም በመናገራቸው ብቻ „ሽብርተኛ“ ብሎ ማሰርና ማጉላላት የወያኔ ባለስልጣናት የሁልግዜ ድርጊቶች ናቸው።በአሸባሪነትና በግዳይነት የሚታወቀው የወያኔ መንግስት ነው። የወያኔ ባለስልጣናት ህዝቡን በየደረጃው በጉቦ ፍዳውን እያሳዩት ነው።ይህም በተለያዩ መስኮች ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ ባለስልጣናት ኪሳቸውን በጉቦ እየሞሉ ያሉበት ሁኔታ ላይ ናቸው።

የወያኔ ባለስልጣናት ለኢትዮጵያ በእርዳታ መልክ ከተገኘው ገንዘብ በሚሊያርድ የሚሆን ዶላር ወደውጭ በማሸሽ፣ በልጆቻቸው ስም ከወያኔው ሕገ-መንግስት ውጪ ተግባራዊ እያደረጉ ነው።ብዙ ዝርዝሮችን ማቅረብ ይቻላል። የወያኔው ጠቅላይ ሚኒስቴር „በሕገ መንግስቱ መሰረት“ ሲል ሲደመጥ ስለነበረ፣ የራሱን የወያኔን ሕገ-መንግስት እየጣሱ ያሉ የወያኔ ባለስልጣናት መኖራቸውን ይገልጻል። የሚችገረው ግን አነዚያ ሕገ-መንግስቱን የጣሱትን የወያኔ ባለስልጣናት በተጠያቂነት ለማቅረብ ወኔው ሊኖረው እንደማይችል ነው።ምክንያቱም በራሱ በወያኔው ጠቅላይ ሚኒስቴር ላይ የወያኔ ባለስልጣናት ይረባረቡበታል። ስለዚህም በመግለጫው ላይ ተጠያቂ የሆኑትን ከነካ እሳቱ እሱንም ስለሚለበልብ ጭጭ ማለትን መርጧል። አሁን ባለንባት የወያኔ ኢትዮጵያ የሕግ የበላይነት የሚሰራው የወያኔን መንግስት ለሚቃወሙ እንጂ ለወያኔ ባለስልጣናት አይሰራም።

**2..** ተጠያቂነትና የወያኔ ባለስልጣናት የወያኔው ጠቅላይ ሚኒስቴር በ 25 ዓመት ውስጥ ከከፍተኛ ችግሮቹ አንዱ ሙሰኝነት እንደሆነ ገልጿል። ችግሩን መግለጹ ጥሩ ነው።ችግሩን የፈጠሩትን የወያኔ ባለስልጣናት ግን በተጠያቂነት ለፍርድ ቀርበው፣ እንዲዳኙ አላደረገም። ይህም ፍላጎቱ እንዳልሆነ ነው። ምክንያቱም የወያኔ ባለስልጣናት በራሱ ላይ ችግር ስለሚፈጥሩበት ብቻ ነው። በዚህ መልኩ ቁጥራቸው በርከት ያሉ የወያኔ ባለስልጣናት አሉ ከሚባሉት ጥቂት ቱጃሮች ተርታ ናቸው።የእነርሱ ልጆች አገርም ውስጥ አይማሩም። ውጪ አገር ተልከው እየተማሩ ነው። ይህም ከሕዝብ በሙስና በተዘረፈ ገንዝብ ነው። የወያኔው ጠቅላይ ሚኒስቴር በምንም መልኩ የወያኔን ባለስልጣናት በተጠያቂነት እንዲቀርቡ የሚደረግበትን ሁኔታ ራሱ የሚፈልግ አይሆንም። ምክንያቱም የወያኔ ባለስልጣናት ተጽዕኖ ይህንን እውን ሊያስደርገው የሚያስችለው አይሆነም።የወያኔውም ፍርድ ቤት የዘራፊዎቹ ማህበር አባል ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን የወያኔ ባለስልጣናት የሚያደርሱበትን በደሎች እየተጋፈጠና እየታገለ ይገኛል።

3. የሕግ የበላይነትና የወያኔ ባለስልጣናት የወያኔው ጠቅላይ ሚኒስቴር ማንም ሰው ከሕግ በላይ እንዳልሆነና የወያኔ መንግስት ሃላፊነት የሕግ የበላይነትን ማስከበር እንደሆነ ደጋግሞ ገልጿል። በተለይ በአማራው ክልል በተነሳው ህዝባዊ እንቅስቃሴ የወልቃይት ጠገዴን ጉዳይ አስመልክቶ የፍጅት አዋጅ በአማራው ላይ ማወጁን በገለጸበት ወቅት ነው።የሕግን የበላይነት የወያኔ መንግስት ማስከበር እንዳለበት አጽንዖት በመስጠት ደጋግሞ ሲግልጽ፣ የወያኔ ባለስልጣናት እያደረጉ ያሉትን የራሱን የወያኔ ሕገ-መንግስት ጥሰቶች ዓይኔን ግንባር ያድርገው እያለ ነው።የወያኔ ባለስልጣናት የራሳቸውን ሕገ-መንግስት እንደፈለጉ መጣስ ይችላሉ። ሌሎች ኢትዮጵያውያን ግን ይህ መብት እንደሌላቸው ነው።የወያኔ ባለስልጣናት ከሕግ በላይ ናቸው።

ለዓባይ ጸሃይና ስዩም መስፍን ማስፈራሪያዎች የወያኔው መንግስት ባለስልጣን አባይ ጸሃዬ ለምን የሩዋንዳውን እልቂት "የወያኔ መንግስት ይወገድ" ለሚለው የሕዝብ ጥያቄ እንደ ቅንጅቱ ምርጫ ግዜ መዘዘው? የወያኔ ባለስልጣናት የህዝቡን ትግል ትኩረት ወደማይረባ የወያኔ ማጭበርበሪያ የፖለቲካ አካሄድ ለመለወጥ እንደሆነ ለማንም ግልጽ ነው። የወያኔ መንግስትና እውሸት ተለያይተው አያውቁም። ዛሬም በተለያዩ የወያኔ ሚዲያዎች የትግራይን ሕዝብ ተከላካይ ሆኖ ለመቅረብ የመሞከር የማጭበርበር ፖለቲካ ነው።የትግራይ ሕዝብ ኢትዮጵያዊ ነው። ወያኔ የትግራይን ሕዝብ ሳይሆን፣ እራሱን ለመከላከል ሲል የትግራይን ሕዝብ ለመጠቀም ይሞክራል። ይህ የተበላ እቁብ ነው።

የወያኔ መንግስት የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠላት ነው። የመንግስት ስልጣኑን ለኢትዮጵያ ሕዝብ አስረክቦ መውረድ አለበት ነው። ሌላ ከዚህ ሁሉ እልቂት በኋላ ወያኔም ሆነ አባይ ጸሃዬና መሰሎቹ የዘረፋችሁትን ብር ይዛችሁ መጥፋት ብቻ ነው። ስለ ሩዋንዳ አባይ ጸሃዬ የሚያወራው ከወያኔ የተሰጣቸውን የኢትዮጵያን ሕዝብ ለማስፈራራት የወያኔ ሆዳሞች ባሁኑ ወቅት እየተጠቀሙብት ያለ የከሰረ ፖለቲካ ነው።ኢትዮጵያውያንን መናቅም ጭምር ነው።የሁሉም መፍትሄ ወይም መድሃኒት ወያኔ ብቻ ነው አባይ ጸሃዬ እያለን ያለው።

100 ሚሊዮን ኢትዮጵያውያንን ማሰብ እንደማይችሉ በመናቅ እያስተጋባ ነው። ይህ የወያኔ ባለስልጣናት ከሕዝቡ ጥያቄዎች ራሳቸውን ለማሸሽና የፈለጉትን ያህል እየገደሉ፣ እያሰሩ፣ አያሰቃዩ ለመቀጠል ዘዴ ነው ብለው ያሰቡት አካሄድ ነው። ስለዚህ የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግሉን ማፋፋምና አንድ ዴሞክራቲክ የሆነች ኢትዮጵያ የዜጎቿን ሁሉ መብቶች በተግባር የምታውልና በፖለቲካው፣ በኢኮኖሚውና በማህበረ ሰባዊ መስኮች ዜጎቿ ያላቸውን መብቶች በተግባር የምታስጠብቅ አገር ለመገንባት ትግሉን መቀጠል ብቻ ነው። የአባይ ጸሃዬም ሆነ ሌሎች የወያኔ ነፍሰ ገዳዮች የጭንቀትና

የተስፋ መቁረጥ ዋይታ ነው።ወደፊትም በሕዝብ ላይ ባደረሱት ጭፍጨፋ ክተጠያቂነት እንደማያመልጡ ያውቃሉ።ስለሆነም ኢትዮጵያን ለመበታተን መፈለጋቸው አይቀርም።

ግን ኢትዮጵያ አትበታትንም።

ኢትዮጵያ በአማራና በኦሮሞ ጠንካራ የተባበረ ትግል የመገንጠል ጥያቄን አስወግደው ሌሎቹንም ኢትዮጵያውያንም በእኩልነትና በኢትዮጵያነት በሰላም ሊኖሩ የሚችሉብትን ሁኔታ ሊያመቻቹ ይገባል።ኢትዮጵያ ከዘር ፖለቲካ ወጥታ ሁሉም በዜግነቱ ፄትም መኖር፣ መስራት፣ መዝናናት፣ መማር፣. . . ወዘተ የሚችልበትና ኢትዮጵያ ለሁሉም ዜጎች ጠቃሚ የሆነች አገር እንደምትሆን ተስፋ ይኖረናል። የወያኔ ባለስልጣናት የራሳቸውን ሕገ-መንግስት ጥሰው ከራሳቸው ሕግ በላይ በመሆን፣ ሕዝቡን እየበደሉት፣ ሕዝቡ ሲበዛበት የወያኔን መንግስት ወጊድ ማለቱ ግን ግዜ ይፍጅ እንጂ አይቀርም። የወያኔ መንግስት ዛሬውኑ ከስልጣን ይውረድ!

**ከተንሳይት በቃና**

ሰፕቴምበር.16 ቀን 2016 ዓ.ም.

http://www.ethiopanorama.com